## ኢትዮጵያ፡- ነጠላ እና ጋቢ

ከሁለት ዓመታት በፊት ለአንድ ጉዳይ አኩስም ሄጄ ነበር፡፡ አንድ የሰባ ሁለት ዓመት ሽማግሌ አገኘሁ፡፡ እናም ስለ አኩስም እና አኩስማውያን እናወራ ጀመር፡፡

«አኩስም ማለትኮ ትንሿ ኢትዮጵያ ናት፡፡ እዚህ ያልኖረ፣ ያልሠራ፣ ያልተቀበረ የሰው ዓይነት የለም፡፡ እስኪ የአኩስም ነገሥታትን ስም ተመልከት የትግሬ ይሁን የአማራ፣ የኦሮሞ ይሁን የአገው በምን ታውቃለህ? እዚህኮ አይደለም ኢትዮጵያዊ ግሪኩ፣ አርመኑ፣ ጣልያኑ፣ ዓረቡ፣ አይሁዱ፣ ግብጹ፣ ሕንዱ፣ ምን ያልኖረና ያልተቀበረ አለ? አኩስም የሁላችሁ ናት፡፡ አኩስም በመወለድ አይደለም በመሆን ነው» አሉኝ፡፡ ገርሞኝ ነበር የማዳምጣቸው፡፡

በተለይ ደግሞ «አኩስም በመወለድ ሳይሆን በመሆን ነው» ያሉት ነገር ለእኔ ትልቅ ፍልስፍና ሆነብኝ፡፡ እንዴት? አልኳቸው፡፡ «አኩስማዊ የምትሆነው አኩስም ስለተወለድክ አይደለም፡፡ አኩስም ተወልደው እንደ ዮዲት ጉዲት አኩስምን ያጠፉ ሞልተዋል፡፡ እነዚህ አኩስማውያን አይደሉም፡፡ አኩስማውያን ማለት በአኩስም ሥልጣኔ የሚሄዱ፣ ለኢትዮጵያ የሚቆረቆሩ፣ ለታሪክ እና ሃይማኖት ክብር የሞቱ ናቸው፡፡ የትም ተወለድ፤ ይህንን ካደረግክ አንተ አኩስማዊ ነህ፡፡

«እኛ አኩስሞች ዘረኛነት አናውቅም፡፡ (እንዲህ ሲሉኝ እጃቸውን ወደዚያ እያወራጩ ነው፡፡) እዚህ ዋናው ሥራህ ነው ትውልድህ አይደለም፡፡ እስኪ እነዚህን የአኩስም ቤተ ክርስቲያኖች ተመልከት፡፡ (ጣታቸውን ወደ አሮጌው እና አዲሱ የቅድስተ ማርያም ቤተ ክርስቲያን አመለከቱኝ) ያንን የጥንቱን ያነፀው ፋሲል ነው፡፡ ከየት እንደመጣ ታውቃለህ? ከጎንደር ነው፡፡ ይህንን ያነፀው ተፈሪ ነው፡፡ እርሱም ከሸዋ ነው የመጣው፡፡ ለኛ ግን እነዚህ ሁሉ አኩስማውያን ናቸው፡፡

ታቦቷ ያለቺበትን መቅደስ ማነው ያነፀው? መነን ናት እርሷም ከሸዋ መጥታ ነው፡፡ በዮዲት የመከራ ጊዜ ሸዋ፣ በግራኝ ወረራ ዘመን ኤርትራ ሄዳ ነው ታቦቷ የቆየቺው፡፡ አሁን ይህንን ሐውልት ማን እንደሠራው በምን ታውቃለህ? ትግሬ ነው? አማራ ነው? ኦሮሞ ነው? አገው ነው? ወላይታ ነው? ሶማሌ ነው? ለመሆኑ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ዘሩ ምን ነበር? አማራ ነው? ኦሮሞ ነው? ትግሬ ነው? ምንድን ነው? ኢትዮጵያዊ ነው፡፡

ስንቶቹ የጎንደር እና የሸዋ ነገሥታትኮ ሥልጣን እጅ ካደረጉ በኋላ እዚህ አኩስም መጥተው ነበር ዘውድ የሚጭኑት፡፡ በዚያኛው በር በኩል አላየኸውም? (በጥንቱ ቤተ ክርስቲያን መግቢያ በር በኩል ነገሥታቱ ሲመጡ የሚቆሙበት፣ የሚቀመጡበት እና በትረ ሥልጣን የሚጨብጡበትን ትውፊታዊ ቦታ ማለታቸው

www.danielkibret.com

ነው) እዚያ ሳይደርስ ማን ይነግሥ ነበር? ለምን ይመስልሃል? ሁሉም አኩስማውያን ናቸዋ፡፡ አኩስማዊነት ማለትኮ ኢትዮጵያዊነት ነው፡፡ ሌላ ነገር የለውም፡፡ እናንተ ባለፈው ጋቢ አልሰጧችሁም? (የአኩስም የቅዱስ ያሬድን ትምህርት ቤት ለማሳደስ በተቋቋመው ኮሚቴ ለሠሩ አባላት እናንተ አኩስማውያን ናችሁ፣ ታሪክ ጠብቃችኋልና ብሎ ሕዝቡ ባህላዊ ጋቢ ሸልሞን ነበር) አየህ አሁን አንተ እዚህ አልተወለድክም፤ አላደግክም፤ አልኖርክም፤ ቋንቋ አታውቅም፤ ግን አኩስማዊ ነህ፡፡ የያሬድ ታሪክ እንዳይጠፋ ብላችሁ አይደለም የሠራችሁት፤ ታሪክ ጠባቂ ከሆንክ አኩስማዊ ነህ ማለት ነው፡፡ ለዚህ ነው ጋቢ የሰጠናችሁ፡፡ እዚሁ ተወልዶ ደግሞ አኩስማዊ ያልሆነ ብዙ አለ፡፡ መወለድ ምን ቁም ነገር አለው፡፡

«አባ ጉራጌን ታውቃቸዋለህ? ከዐፄ ዮሐንስ ሠራዊት ጋር አብረው እየዘመቱ ወታደሩን በርታ ጠንክር እያሉ ለሀገሩ እንዲዋጋ ያደፋፈሩት አባ ጉራጌ እዚህ አኩስምኮ ነው የኖሩት፡፡ በጉራዕ እና በጉንዳጉንዲ ጦርነት ንጉሡን ተከትለው ስንት ውለታ ሠርተዋል መሰለህ፤ አኩስማዊ እኮ ናቸው፡፡ ትውልዳቸው ጉራጌ በመሆኑ ግን ሕዝቡ አባ ጉራጌ ይላቸዋል፡፡

ይህ የአረጋዊው ትምህርት ትዝ ያለኝ አንዳንድ መጽሐፎቻችን እና ጽሑፎቻችን አኩስምን ከአካባቢ፣ ከቋንቋ እና ከአንድ ወገን ጋር ማያያዝ እንደ ጀመሩ ሳይ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሥልጣኔ መገለጫዎች የሆኑ ምእራፎች እና ቦታዎች አሉ፡፡ አኩስም፣ ላሊበላ፣ ጎንደር፣ ሐረር፣ አዲስ አበባ፣ ሌሎችም፡፡ እነዚህ ቦታዎች እና ሥልጣኔዎች በዚያ ዘመን ኢትዮጵያውያን የተገናኙበት ቦታ እና ሥልጣኔ ማዕከል አድርገው እንደነበሩ የሚ ያሳዩ እንጂ ዛሬ በአካባቢው ያሉትን ሕዝቦች ታሪክ እና ሥልጣኔ ብቻ የሚያሳዩ አይደሉም፡፡

አኩስምን ከትግራይ፣ ላሊበላን ከአገው፣ ጎንደርን ከአምሐራ፣ ሐረርን ከሐረሪ፣ አዲስ አበባን ከኦሮሞ እና አምሐራ ጋር ብቻ እያያያዝን የምናያቸው ከሆነ በኢትዮጵያ ታሪክ እና ጉዞ ውስጥ ይቅር የማይባል ስሕተት እንሠራለን፡፡

ለመሆኑ ጎንደር ላይ ስንቱ አልፏል? እነ ራስ ሚካኤል ስሑል ጎንደር ተወልደው ጎንደር ነበር እንዴ ያደጉት? ከትግራይ የመጡ መሳፍንት አልነበሩምን? ደረስጌን ያሳመሯት ራስ ውቤ የትግራይ ሰው አልነበሩምን? እነ ራስ ጉግሳ እነ ራስ ዓሊ፣ ኦሮሞዎች አልነበሩም?

ጎንደር የሀገሪቱ የትምህርት፣ የአስተዳደር እና የሥልጣኔ ማዕከል በመሆንዋ ወደ እርሷ የማይጎርፍ አልነበረም፡፡ እንኳንና ኢትዮጳያውያኑ ቀርተው የውጮቹ ሰዎችም እዚያው ኖረው እዚያው ተጋብተው እዚያው ቀርተዋል፡፡ የእንግሊዛዊው የፐላውዴን መቃብርኮ ጎንደር ግምጃ ቤት ማርያም ነው ያለው፡፡ ጎንደሬው፡፡

ጎንደር መላው ኢትዮጵያ አንድ ሆኖ ላቡን እና ደሙን አዋጥቶ የሠራት የሥልጣኔ ማዕከል ናት፡፡ በግራኝ ወረራ ጎንደር እና አካባቢዋ ከጠፉ በኋላ በዐፄ ሠርፀ ድንግል ጊዜ እንደገና ስታንሠራ ጎንደር ሊቃውንትን ያስመጣቿው ከጉራጌ ነበርኮ፡፡ በደቡብ ጎንደር ሀገረ ስብከት ላይ ጋይንት ወረዳ በደራ ቀፎዬ ገበሬ

ማኅበር የምትገኘው የደብረ ማርያም ገዳም ታሪክ እንደሚገልጠው አባ መሰንቆ ድንግል፣ አባ ለባዌ፣ አባ ብእሴ ሰላም እና መምህር ተክለ ወልድ የተባሉ ሊቃውንትን ከጉራጌ ምሁር ኢየሱስ አምጥተው በጎንደር አድባራት መደቧቸው::

ጎንደርን የትምህርት ማዕከል ያደረጓት እነዚህ አራት የጉራጌ ሊቃውንት ናቸው:: የእነርሱ ደቀ መጻሙርት ነበሩ በመላዋ ጎንደር እና በመላዋ ኢትዮጵያ ተሠማርተው ሀገራዊውን ዕውቀት ከሞተበት ያሥነሡት:: አሁን ጉራጌን ጎንደር ላይ ማን ያስበዋል?

የይምርሃነ ክርስቶስን እና የደብረ ብርሃን ሥላሴን አሠራር ያየ ወሎዬ እና ጎንደሬ አንድ ላይ ሆነው የሠሩት እንደሆነ ይመሰክራል:: የደብረ ብርሃን ሥላሴ ታቦት እና ስም ከሸዋው ደብረ ብርሃን ሥላሴ ሲወሰድኮ ታላቁ ኢያሱ ሁለት ሺ መክሊት ወርቅ ለደብረ ብርሃን ሥላሴ ከፍለው ነው::

ጎንደርን ጎንደር ካሰኟት ሊቃውንት አንዱ የሆነው የቅኔው ባላባት ክፍለ ዮሐንስኮ የአገዎች ምድር ከነበረቺው ከመተከሏ ጋፍኒ ልደታ የተገኘ «ጎንደሬ» ነው:: የአባቱም ስም ቼሐይ ነው:: ሊቁ ክፍለ ዮሐንስ ከብቃቱ የተነሣ የሥላሴን በዓል በጎንደሩ እና በሸዋው ደብረ ብርሃን ሥላሴ እየተገኘ በአንድ ቀን ያከብር ነበር ይባላል:: ለዚህም ነው

እነሂ ወግብረ ቅኔ ዘበሆሳዕና

እም ዕደ ገፋዒ ወተገፋዒ ንትመሰጥ በደመና

ያለው እያሉ ሊቃውንቱ ይተርኩለታል::

እንኳን እና ሰው የጎንደር ታቦታት እንኳን ከመላዋ ኢትዮጵያ ተሰብስበው ጎንደር የከተሙ ናቸው:: የጎንደሩ አደባባይ ኢየሱስ በዐፄ ሠርፀ ድንግል ዘመን ወደ ጎንደር ተሻግሮ የተተከለ የወላይታ ታቦት ነው:: የአዞዞ ተክለ ሃይማኖት ታቦታት ከሸዋ ደብረ ሊባኖስ የሄዱ ናቸው:: ኤርትራዊው አቡነ ኤዎስጣቴዎስ አርመን ተጉዘው ካረፉ በኋላ ዐፅማቸው መጥቶ ያረፈው ጎንደር መንበረ መንግሥት መድኃኔዓለም ነው::

በጎንደር አድባራት እየዞርን የሊቃውንቱን እና የመምህራኑን ስም እና የዘር ሐረግ ብናጠና በከተማዋ እና በአካባቢዋ ተወልደው ካደጉት ይልቅ ከጎጃም፣ ከሸዋ፣ ከትግራይ፣ ከወሎ፣ ከሐረር፣ ከኤርትራ፣ ለትምህርት መጥተው እዚያው ለምደው እዚያው የቀሩት ይበልጣሉ:: ሀገሬው ትምህርታቸውን እና ደግነታቸውን ተመልክቶ ልጁን ድሮ በዚያው ርስት እያሰጠ ያስቀራቸዋል:: ጎንደር ላይ አገልግለው ጎንደሬ ይባላሉ::

እነዚህ ሁሉ የሀገሪቱ ልጆች ጎንደር ላይ ሲያንጹ፣ ጎንደር ላይ ሲጽፉ፣ ጎንደር ላይ ሲቀኙ፣ ጎንደር ላይ ሲያዜሙ፣ ጎንደር ላይ ሲነግሡ፣ ጎንደር ላይ ሲሾሙ ለሀገራቸው እና ለወገናቸው አንዳች ነገር ስለማድረግ ያስቡ ነበር እንጂ ለጎንደር ወይንም ለአማራ ብለው የሠሩት አልነበረም::

ሸዋ እንውረድ እስኪ፤ አዲስ አበባ የማናት? የአዲስ አበባ ሥልጣኔስ የማነው? አዲስ አበባ ላይ ወዝ እና ደሙ ያልፈሰሰ ኢትዮጵያዊስ አለ? የአዲስ አበባውን የእንጦጦ ራጉኤል ንድፍ ያወጡት «ዘጠኙ ጎንደሬዎች» የሚባሉት ከጎንደር የመጡት አርክቴክቶች አልነበሩም እንዴ? የድንጋይ ባለሞያዎቹ አንኮበሬዎች ሲሆኑ እነ አፔንዚለር እና አልፍሬግ ኢልግ የተባሉት ስዊድናውያን እነፃውን አብረው ሠርተዋል።

እነ ሐጂ ቀዋስን የመሰሉ ሕንዳውያን ደግሞ በዋና አርክቴክትነት ከጎንደሬዎቹ ጋር ሠርተዋል። እንጨቱ ከመናገሻ፣ ቆርቆሮው ከፈረንሳይ፣ የጣርያው ርብራብ ከካይሮ መጣ። ታቦቱስ ቢሆን የጎንደር ታቦት አይደለም እንዴ? ሰዓሊዎቹ አለቃ ዮሐንስ ዘጎንደር ማኅደረ ማርያም፣ አለቃ ሉቃስ ዘጎጃም፣ አለቃ ሣህሉ ዘጎጃም ነበሩ። እስኪ እንዴት ሀገር አንድ ሆኖ እንደተባበረ ተመልከቱ።

ታላቁ ካቴድራል ቅድስት ሥላሴ ታቦቱ የመጣው በግራኝ ጊዜ ከፈረሰው ከወሎው መካነ ሥላሴ ነው። ከዚያ ተወስዶ ወግዳ ኖረ፣ ከወግዳ ራስ ጎበና አምጥተው ሸዋ አዲስ ዓለም ፍየታ አኖሩት። ምኒሊክ ደግሞ አዲስ አበባ አራት ኪሎ አመጡት።

አዲስ አበቤ ማለት ምን ማለት ነው? አዲስ አበባ የኖረ ማለት እንጂ የተወለደ አይደለም። የአዲስ አበባን አብያተ ክርስቲያናት፣ መስጊዶች፣ መንገዶች፣ አብያተ መንግሥት፣ ሕንፃዎች፣ ት/ቤቶች የሠሩት የኢትዮጵያ ልጆች ናቸው። ያንን ሲሠሩ ለሀገራቸው አንዳች ነገር እንደሠሩ ያስቡ ነበር እንጂ ለሸዋ ወይንም ለኦሮሞ ሲሉ አልሠሩትም።

ዛሬ የሐረሩ ቁልቢ ገብርኤል ታቦት የጥንቱ ከአኩስም ትግራይ የዛሬው ከሸዋ ቡልጋ የመጣ ነው ቢባል ማን የሐረር ሰው ያምናል? ልክ ደቡብ ሸዋን እና ወለጋን የሰበኩት አቡነ ሳሙኤል ዘደብረ ወገግ ከሐረር ነው የመጡት ቢባል ወለጌ እና ሸዬ እንደማያምነው ማለት ነው። የመጀመርያው የቁልቢ ታቦት መነሻውን አኩስም አድርጎ ከታቦተ ጽዮን ጋር ዝዋይ መጣ። ታቦተ ጽዮን ስትመለስ እርሱ ዝዋይ ቀረ። አባ ሌዊ አምጥተው ቁልቢ ዋሻ ውስጥ አስቀመጡት።

ሌላም የሚገርም ይህቺ ሀገር እንደ ዘሐ ዘጊ የተያያዘች መሆንዋን የሚያሳይ ታሪክ ልጨምር። በግራኝ አሕመድ ወረራ ዘመን መልአከ ገነት መብረቁ፣ መምህር የማነ አብ፣ አባ ተከሥተ ሥሉስ የተባሉ አበው ወደ ቁልቢ ይሄዳሉ። በዚያም በድንጋይ ላይ አባ ሌዊ የጻፉትን የቁልቢ ታሪክ ያገኛሉ። ከቁልቢ ሲመለሱ ያንን በመጽሐፈ ቀሌምንጦስ ኅዳግ ላይ ገልብጠው በደሴተ ዝዋይ አስቀመጡት። ራስ መኮንን ከዝዋይ ደሴት መጽሐፈ ቀሌምንጦስን አስመጥተው ሲያነቡ ታሪኩን አገኙ።

በቦታው ላይ ሌላ የገብርኤል ታቦት ለማስገባት ፈልገው ሲያፈላልጉ ቡልጋ ላይ ያገኙታል። እነሆ ዛሬ የሐረርጌ አንዱ መታወቂያ ሆነ።

ኢትዮጵያን ዛሬ ዘመናችን ባመጣብን ጎጠኛ አስተሳሰብ ማየት የለብንም፡፡ ኢትዮጲያ ከዚህም የሰፋች የተለየቺም ናት፡፡ ሰሎሞን ደሬሳ «በጥንት ሴት አያቶቼ በር ማን እንዳለፈ አላውቅም» እንዳለው ከዚህኛው ዘር ብቻ እወለዳለሁ ብሎ መናገር የዋሕነት ሳይሆን አላዋቂነት ነው፡፡ ይህኛው ወይንም ያኛው ሥልጣኔ እና ታሪክ፣ ገድል እና ተአምር የዚህ ወገን ብቻ ነው ብሎ መጻፍም ኢትዮጵያን አለመረዳት ነው፡፡

ኢትዮጵያኮ እነ አቡነ አረጋዊ ከአውሮፓ፣ እነ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ከግብጽ፣ እነ እጨጌ ዕንባቆም ከየመን መጥተው ኢትዮጵያዊ የሆኑባት ሀገር ናት፡፡ እንዴት ነው አንድን አካባቢ ዛሬ በቦታው ለሚኖረው ሕዝብ ብቻ መስጠት የምንችለው? ተዋግተንም፣ ተፋቅረንም፣ ተጣልተንም፣ ተዋልደንም፣ ተጋፍተንም፣ ተሳስበንም አሁን ያለውን መልክ ይዘናል፡፡ ዛሬ ያለው መልክዐ ምድር ጦርነት የፈጠረው መልክዐ ምድራችን ነው፡፡ ኢትዮጵያን እንደ ጦርነት እና የሃይማኖት ንቅናቄ አንድ ያደረጋት ነገር ያለ አይመ ስለኝም፡፡ አንዳችን ማግ ሌላችን ዝሐ ሆነን አሁንማ ነጠላ እና ጋቢ ሆነናል፡፡

www.danielkibret.com